# ወይ ዋሽንግተን ወይ DC ሆይ፤
# ከነ ታማኝ ሌላ ሰው የለሽም ወይ??

አንዳንድ የመድረክ ሰዎች ከየነቢጤው የጥበብ አፍቃሪ በየመድረኩ በአድናቆት የሚወዛወዝ ጭንቅላት፣ ፍዝዝ .... ቅዝዝ ብሎ የሚመለከታቸው አይን፣ በደስታ የተዋጠ ሞቅ ያለ ጭብጨባ፣ በስሜት የተሳከረ ሙገሳ፣ በቅርብ የማወቅ ጉጉት፤ መወደድ፣ መከበር፣ መፈቀር፣ ..... ዝና ...... ሲሰጣቸው በፖለቲካዊና ማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ “አፍሳይት” ገብተው ከኛ በላይ ላሳር ማለትን ያመጣሉ።

“አርቲስቶቻችን” ያልተረዱልን ነጥብ ያለ ይመስለኛል። አርቲስት ማለት በየነቢጤው የመድረክ ታዳሚ እጅ በማንኪያ የተያዙ እንቁላል መሆኑን።

የቦስተኑ አቡጊዳ ቴሌቪዥን ከመድረኩ መሪ “አርቲስት” አቶ ታማኝ በየነ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ ተከታተልኩት። አቶ ታማኝን "ጋዜጤኛው" ያጎናፀፋቸውን “የአርቲስት እና የሰብአዊ መብት ተሟጓች” ክብርና ማዕረግ ላፀድቅላቸው ባለመቻሌ አስቀድሜ በኢትዮጵያዊ ትህትና ይቅርታቸውን እጠይቃለሁ።

የዚህ ፁሑፍ አቅራቢ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ትግል ተካሂዶ የበለፀገች ኢትዮጵያን ማየት ይመኛል። “ **Development is the struggle of opposites”** የሚለውን ቀላል ፍልስፍና ይቀበላልና ነው።

አቶ ታማኝ "በልጅነታችን መንግስቱ ወርቁን ... አበበ ቢቂላን .... ጥላሁን ገሰሰን ለመሆን ስንመኝ እንጅ እንደ እገሌ ፖለቲከኛ ለመሆን የሚያሰኝ ጥሩ ምሳሌ ሆኖ ስሜታችን የሚጭርልን ሁኔታ አልነበረም" ብለዋል። በዚህ ነጥብ እኔም እስማማለሁ። አዎን!! ሰው ፈጣሪው ፊት የቀረበ እስኪመስል ድረስ መሬት እስኪነካ ሲያጎነብስ፤ ሒላም ’ይወድማል’ እየተባለ ክንድ ሲታጠፍና ሲዘረጋ እንጅ አማራጮችን በማቅረብ እኔ የተሻልኩ ነኝ .... እኔን ምረጡ ሲባል አንሰማም ነበር። ታዲያ በህዝቦች መስዋእትነት በተፈጠረ መድረክ ፖለቲከኞች እኔ ... እኔ ... ሲባባሉ ዛሬ ማየቱ ራሱ ትንሽ ’ክሬዲት’ አያሰጥም እንዴ?

አቶ ታማኝ ’ዲያስፖራውን’ በሚመለከት በተለይ አሜሪካ ያለውን አበሻ “በሰለጠነው አገር እየኖርን የልሰለጠንነው እኛ ነን” ሲሉ ተችተዋል። በጅምላ መወረፍ እኮ ያስገምታል። በቅርቡ አሜሪካ ውስጥ ያለውን ኢትዮጵያዊ ስደተኛ በማስመልከት ከቦስቶኑ ’አራዳ ሬዲዮ’ ጋር ቃለ ምልልስ ያደረጉት ምሁር በተለያዩ ወቅት ከእረኛ እስከ ፕሮፌሰር ድረስ ወደ አሜሪካ መጥተዋል ብለዋል። ታዲያ አቶ ታማኝ ሁላችንንም ለመኮነንና በድፍረት ለመናገር ሞራላዊ፣ አካዳሚያዊ፣ ሆነ ፖለቲካዊ ብቃት ያላቸው አይመስለኝም። ምክንያቱም አቶ ታማኝ በየመድረኩ ሲኮንኑ ነው እንጅ ዲያስፖራውን በሚመለከት ጥናትና ምርምር ሲያካሂዱ የታዩበት ዘመን የለምና።

"ስድብ የኢትዮጵያዊያን ባህል አይደልም" ያሉን የመድረኩ ሰው ዕድሜ ለአቡጊዳ አዘጋጆች **Washington DC** ውስጥ ይመስለኛል ተፅፎ በተዘጋጀና ለሁለተኛ ክፍል ተማሪ በማይመጥን ግጥም 'አርቲስት' ታማኝ የኢትዮጵያን መሪዎችን ስም እየጠሩ 'በአያሆሆ ..... ማታ ነው ድሌ ጭፈራ ሲሳደቡ ማየቴ 'አጃኢብ' አስኝቶኛል።

ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ፤ አለ ያገሬ ሰው! አቶ ታማኝ ኢትዮጵያዊ አይደሉም እንዴ? ነው ወይስ ጠቀም (ወፈር) የለ ክፍያ ስላልነበረ ነው በተራ ስድብ መድረክ ላይ ከ 'Hero to Zero' የወረዱት።

ምነው አቶ ታማኝ? ብዙዎች መሪዎች ንግግር ፀሀፊ (speech writer) ባለሙያ አላቸው። እርስዎም ለመሳደብ ይከፈልዎት ከሆነ በእውነቱ እርስዎ የመጀመሪያው (pioneer) ባለ ሙያ መሆንዎ ነው። Guiness Book of Records ላይ ስምዎ መፃፍ ነበረብዎት።

ስለ ትግራይ፡ ኢትዮጵያዊነትና ስለ ወያኔ ሰፋ ያለ ትንተና ያስደመጡን አቶ ታማኝ ብዙ ሳይቆዩ ጀግኖቻችንን በስም እየጠሩ 'እምቢ ባለ ነው መይሳው' ... 'እምቢ ባለ ነው ሚኒሊክ' .... 'እምቢ ባለ ነው በላይ፡' እያሉ ታሪክ ነገሩን። በርግጥ አቶ ታማኝ የእስራኤላዊው ሃጋይ ኤርሊክ መፅሐፍ ለማንበብ ራሳቸው እንዳሉት 'ልሙጥ መሃይም' ቢሆኑም አፄ ዮሐንስ 'እምቢ ባለ ነው ዮሐንስ' ለመባል ከአቶ ታማኝ አይጠበቁም። አቶ ታማኝ ፈለጉም አልፈለጉም የኢትዮጵያ ህዝብ አፄ ዮሐንስን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተገቢውን ቦታ ይሰጣቸዋል።

"ልሙጥ መህይም" መሆናቸውን በተደጋጋሚ የነገሩን አቶ ታማኝ የዓድዋ ድል በማስመልከት ባቀረቡት 'ልሙጥ ትንታኔ' ሰዎችን በመጥቀስ 'የዓድዋ ድል ታሪክ ሆዳም ምሁራኖች ያዘጋጁት ቲያትር አይደልም' ለማለት እውቀቱን ከየት እንዳገኙት በበኪሌ ገርሞኛል። ዓድዋ የኢትዮጵያ ህዝቦች በዳግማዊ ምኒሊክ መሪነት አንፀባራቂ ድል ያስመዘገቡበት የአባቶቻችን የነፃነትና የአልገዛም ባይነት ገድል እንጅ ቲያትር እንዳልሆነ ለቲያትር መድረክ ቅርብ የሆነና 'አርቲስት' ነኝ የሚል የሚዘነጋው አይመስለኝም። “እንኳን ምኒሊክ ... ብራዚል እንኳ ዋንጫ ያገኘው በሮማሪዮ ነው” ማለታቸው “በምናገረው ነው የምከፈለው” ... 'እንጀራየ አንደበቴ ነው' ላሉት አቶ ታማኝ ብራዚልና የዓድዋ ድልን ማዛመድ ለምን እንደፈለጉ ባይገባኝም ተመፃዳቂ ( **high – flier)** ብቻ ሳይሆን ቁምነገራቸው ትርጉምየለሽ **(abaracodabra)** ሆኖ ነው ያገኘሁት።

አቶ ታማኝ አዎ! እርሰዎ እንዳሉት ድህነት ያሳፍራል። መድረክ ላይ ስም እየተጣሩ መሳደብም ያሳፍራል። በተለይ በርስዎ 'በአርቲስት' አንደበት።
አቶ ታማኝ! በርስዎ እድሜ ያለ ስው እኮ በአሁኑ ስዓት መድረኩን 'ለፕሬዘዳንትነት ምረጡኝ እየተጠቀሙበት ነው።

አቶ ታማኝ የሻቢያ ሰራዊት ሉአላዊነታችንን በደፈረበት ወቅት የጥበብ ባለ ሙያዎችን በማሰባሰብ ከፍተኛ አስተዎፅኦ ማድረጋቸው ጋዜጠኛው ገለፀልንና ብዙ ሳይቆይ ግና 'እኔ ወያኔዎችን የምቃወመው አያት ... ቅድመ አያቴ የተቀበሩበትን

አገር አጥር ሲያፈርሱ ነው 'ሲሉ አቶ ታማኝ ገለፁልን። ጎበዝ! እንዴት ነው ነገሩ? በበኩሌ አቶ ታማኝ ዜግኔታዊ ግዴታቸውን ተወጠዋል ባይ ነኝ። ሆኖም አጥር ሲየፈርስ ያፈረሰው እኮ ሻቢያ መሰለኝ.... እየ ተስተዋለ እንጅ!!!

የመድረክ ሰዎች! ከኪነጥበባዊ ሞያዊ ውጭ በፖለቲካዊና ማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ ባትገቡስ? እንዴ! እኛ እኮ ያለእናንተ መኖር እንችላለን እናንተ ግን .....

DC ያላችሁ የኛ ሰዎች ..... ጥዋት ማታ ስትሰለፉ .... ስትጮሁ ..... ስትኮንኑ ባንዲራችንን ከፍ አድርጋችሁ ስታውለበልቡ ሳይ የአዲስ አበባውን አብዮት አደባባይ ያስታውሰኛል።አብዮት አደባባይ ላይ የተሰነዘረው ጡንቻ .... የተጮኸው ... የተፃፈው መፈክር .... የተሰነጠቀው ጉሮሮ .... ሰልፍ .... ውጤቱ ምን ሆነ? ምንም ታዲያ!! DC ላይ ይህንን የምንደግመው ለምን ይሆን? "ውሾቹ ይጮሀሉ .... ግመሉ ግን ጉዞውን ቀጥሏል 'ሲባል አልሰማን ይሆን? እንዲያው ግና ከዚያ ከDC  በሳል የፖለቲካ አዋቂ ወጥቶ ሁላችንንም አሰባስቦ የተሻለ የዕድገት አቅጣጫ ቀይሶ በዚህ_በኩል የሚል ሰው ላይገኝ ነው እንዴ? ውቧ DC የሁከት የውድቀት .... የጩኸት .... የኪነኔ ... መድረክ ሁና ትቅር?

ነገሩ ነው እንጅ እዚህ ሆነን አውርደን ለምንሰቅለው .... ሹመን ለምንሽረው ... ለምንጮኸው ከምእተ ዓመታት በፊት አፍሪካዊ ጀነራል ብለውታል። "ከሩቅ የሚጮህ ዉሻ አይናከስም'።

አቶ ታማኝ በተለያዩ ነጥቦች ዙሪያ ብዙ ብለዋል። እኔም ብዙ ባልኩኝ ነበር። ምን ዋጋ አለው? የሆነ ሆኖ መድረክ በመምራትና አገር በመምራትመካከል ትልቅ ልዩነት አለና አቶ ታማኝ መልካም ፍቃዳቸው ሆኖ የአገራችን ብሂል ይቀበሉኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ። የአገሬ ሰው እንደ እርስዎ አይነት ሰው ሲያጋጥመው ' ጫማህ በእግርህ ልክ ነው'  'ሳእንኻ ማዕረ እግርኻ'  እንግሊዘኛ ተናጋሪዎች ደግሞ 'Cut one's coat according one's size' እንደሚሉት ይላልና!!!

**ወይ ዋሽንግተን ወይ DC ሆይ፣**
**ከነ ታማኝ ሌላ ሰው የለሽም ወይ**

ናኦድ ከቦስተን